# ያ ትውልድ

የ«ያ ትውልድ ተቋም» ልሳን

ያ ትውልድ ቅጽ 8 ቁጥር 4 ሚያዝያ 23 ቀን 2013 ዓ.ም.

## ከሜይ ዴይ ሰማዕታት እስከ ዘር ፍጅት በኢትዮጵያ

*(የድምጽ ቅጅውን ለማድመጥ ሊንኩን ይጫኑ https://www.youtube.com/watch?v=pTLCgLLbZp4 )*

ለክርስትና እምነት ተከታዮች በሙሉ እንኳን ለብርሃነ ስቅለቱና ለፋሲካ በዓል በሰላም አደረሳችሁ እንላለን። ባህላችን ሆነና "ሰላም ያሳደርከኝ አምላኬ በሰላም አውለኝ" እንላለን። የእምነት በዓላት ሲመጡ ደግሞ "እንኳን አደረሳችሁ" እንባባላለን። ዛሬ ሀገራችን ኢትዮጵያ ካለችበት ዘግናኝ ሁኔታ አንጻር በየጊዜው የሰው ልጅ እልቂት አየሩን በሞላበት ሰዓት፣ መሽቶ እስኪነጋ ምን ሊከሰት ስጋት በሆነበት ወቅት የእምነት ባህላችን ከደስታውና ከእንብላው፣ እንጠጣው ባሻገር በክርስትና እምነት ተከታዮች ዘንድ "እግዚአ መሃረነ ክርስቶስ፣ በእንተ እግዚትነ ማርያም መሃረነ ክርስቶስ፣ ደጉን ዘመንና ጊዜ አምጣልን" የምንልበት ሲሆን በሙስሊሙም ኅብረተሰብ ዘንድ "ወአላህ ክበር" እያልን በተያዘው የጾም ወቅት በየቀኑ የሚሰገድበትና "በቃ በለን አላህ" በማለት ጁምአ የሚካሄድበት ወቅት ነው።

ከፖለቲከኞች አንጻር፣ ከያ ትውልድ አኳያ ደግሞ ዛሬ ሚያዝያ 23 ቀን 2013 ዓ.ም. "እንኳን ለዓለም ሠራተኞች ቀን ሜይ ዴይ አደረሳችሁ" እንላለን። ስለ ሰው ልጅ፣ ስለ ሀገራችን በዓሉን ስናያይዘው ኢትዮጵያችን ወዴት እየሄደች ነው? ያሰኘናል። ኢትዮጵያችን በአለፉት 50 ዓመት ያስመዘገበችው እድገት ቢኖር ረሃብና የሕዝብ ብዛት ሆኖ ይታየናል። ሌላው እድገት ካልነው እሥር፣ እንግልት፣ ስደት፣ እና አስከፊው የሰው ልጆች እልቂት ሁኖ ይታየናል።

ጥንት በንጉሱ ዘመን በላይ ዘለቀን፣ ሃምሳ አለቃ አያሌው እና ሌሎች ሲገደሉ ጉድ የተባለለት ዘመን፣ ወንድማማቾቹን ግርማሜ እና መንግሥቱ ነዋይን በስቅላት አንጠልጥሎ ሥልጣኑን ሊያራዝም ቢፈልግም ግድያና ማስፈራራት ይበልጥ ብሶት እየወለደ ለንጉሡና ለሥርዓቱ መውደቅ ተጨማሪ ምክንያት ሆነ። አቤ ጉበኛን ለግዞት፣ አሳምነው ገብረወልድን ለሞት ያበቃው የሥልጣን አትንኩኝ ባይነት ከተማሪው እንቅስቃሴ ለአብነት በአደባባይ ጥላሁን ግዛውን ገድሎ ማርታና ዋለልኝን አሰውቶ ሥርዓቱ መጨረሻው ውድቀት ሆነ። ለመብትና ነጻነት የተከፈለው መስዋዕትነት የሚያስመዘግበው የአገዛዝ ለውጥ በየጊዜው እሥር፣ ሥቃይ፣ ስደት፣ ግድያ እተቆራኘ ሀገራችን ከአስመዘገበቻቸው የእድገት ደረጃዎች ላቅ ይላል።

ዳግሞ ለመጻፍ እና ለመናገር፣ በየሶሻል ሚድያው የሚለቀቁትን በሙሉ ዓይን ለማየት በሚዘገንን ሁኔታ ዛሬ የሰው ልጅ ሲታረድ፣ ሲቆራረጥ፣ ሲቃጠል ማየት፣ መስማት "ምኑን አመጣብን?" እስክንል አንድ ከተማ ሲወድም ማየት የየዕለት ተግባር የሆነበት የዘር ፍጅት ላይ ደርሰናል።

እኛ የያ ትውልድ አካላት እሥር፣ ግርፊያ፣ ስደት፣ ግድያ ዳግም እንዳይደገም "በእኛ ያብቃ" ብለን ድምጻችንን ብናሰማም አገዛዞች እጆቻቸውን ለፍትህ አልዘረጉምና አንዱ አገዛዝ ከሌላው እየከፋ ሀገራችን ወዴት እየተጓዘች እንደሆነ ግራ እስኪያጋባን ድረስ የሰው ልጅ እልቂት ተለመደና መታረዱ፣ መቃጠሉ ሳይሆን "ስንት ሰው አለቀ?" ወደ ሚለው ተሰበናል።

የዛሬ 44 ዓመት አርብ ሚያዝያ 21 ቀን 1969 ዓ.ም. በኢትዮጵያ የጭፍጨፋ እና የግድያ ዘመን ከየካቲቱ 12 የጣልያን የግፍ ጭፍጨፋ ቀጥሎ በአስደንጋጭነቱና በመሪርነቱ ግዙፍ ነበር ቢባል ማጋነን አይደለም። በደርግ አምባገነናዊና አረመኔያዊ አገዛዝ የተቃውሞ ድምጻቸውን የላብ አደሩን ቀን ምክንያት በማድረግ ሊያሰሙ በወጡ ታዳጊ ሕጻናትና ወጣቶች ላይ ጥይት ተርከፈከፈ። ወጣቶች በየወንዙ፣ በየጉራንጉሩ፣ በየአስፏልቱ በደርግ ጥይት ተረፈረፉ። ከሰላማዊ ሰልፉ ግድያ አምልጠውና ሸሽተው ሕይወታቸው የተረፈው በዕለቱ ለሊቱን ከቤታቸው እየተለቀሙ ተረሸኑ። በአዲስ አበባ የተለያዩ አካባቢዎችና በየጫካው 20 እና 30 እየሆኑ ለሊቱን በጅምላ ተረሸኑ። አስከሬናቸው ለሊቱን ቅድሚያ ለጅብ ተተወ። በማግስቱ ከጅብ የተረፉት እየተሰበሰቡ በጅምላ መቃብር ደርግ ቀበራቸው። በሰልፉ ወቅት የተገደሉትንና ወደ ምኒልክ ሆስፒታል የተወሰዱትን አስከሬኖች ለቤተሰብ በመክልከል በባህላችን የሌለ ሌላ ግፍ ተሰራ። እናቶች በእምቡጥ ልጆቻቸው እልቂት የእብደት ያህል ተቃወሱ፣ አባቶች ተስፋቸው ተሟጠ አቀረቀሩ፣ ጉዳዩ ያልተገለጠላቸው ሕጻናት ፈዘዙ፣ የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ወጣቶች ሊግ (ኢ.ሕአወሊ) ወጣት አባላት ግራ ገባቸው፣ ተደናገጡ። ስለ ዴሞክራሲያ መብት፣ ስለ ሕዝብ መንግሥት አስፈላጊነት ድምጻቸውን ባሰሙ ምላሹ አውሬያዊ ፍጅት፣ ግድያ ይሆናል ብለው አልጠበቁም፣ አልገመቱም ነበርና ሀዘንና ቁጭቱ አስከፊ ነበር።

ፋሽስቱ መንግሥቱ ኃይለማርያም ሚያዝያ 6 ቀን 1969 ዓ.ም. በአብዮት አደባባይ "የኢሕአፓን ደም እንጠጣዋለን" በሚል በደም የተሞላ ጠርሙስ ከአስፏልት አጋጭቶ "ቺርስ" ያለውን በተግባር አሳየ። የወጣቶችን ደም በጅምላ ጠጣ። በርካታ ቤተሰቦችን ልጅ አልባ አደረገ፣ ነጠላ አስዘቀዘቀ፣ ጥቁር አስለበሰ። ልክ የዛሬ 44 ዓመት!

"ያ ትውልድ ተቋም" ዛሬ የፋሲካን በዓል ስናከብር የበሬ እርድና ቅርጫ፣ የምሽት ዶሮ መባረክ ይበልጥ የሚታየን የእኛ ትውልድ ልጆች፣ የሜይ ዴይ 69 ሰልፈኞች እልቂትና ደም ነው። የትግል ደም፣ የእምነት ደም፣ የመብት ደም፣ የሕዝብ ደም፣ የሀገር ደም። ዛሬ የዚያ ጊዜ ዘመን ልጆቻቸውን ያጡ ቤተሰቦች እንደየእምነታቸው የረመዳን ጾማቸው፣ የፋሲካ ባህላቸው በሀዘን የተሞላ፣ በትካዜ የተዋጠ ወደ 44 ዓመት መለስ ብለው ወላጆች ልጆቻቸውን፣ ሌሎች ወንድሞቻቸውን፣ እህቶቻቸውን፣ እኛም የትግል አጋሮቻችንን የምናስብበት፣ የምንዘክርበት ወቅት ነው። "ክብር ለሜይ ዴይ 1969 ሰማዕታት!" እንላለን ከ"ያ ትውልድ ተቋም"።

የደርግ ግድያ አድማሱንና ግዛቱን እያሰፋ በከተሞችና በገጠር ከቤት ለቤት አሰሳ ወደ ነጻ እርምጃ ተሻግሮ በቀይ ሽብር አንድ ትውልድ አሟጦ በታሪክ ጥቁር ነጥብ ጥሎ ያለፈ ፋሽስታዊ አገዛዝ ነበር የምንለው ለዚህ ነው። መንግሥት ዘላለማዊ አይደለምና የ17 ዓመቱ የግፍ አገዛዝ ቢያበቃም "ከዝንጀሮ ቆንጆ ምን ይመራርጠዋል" ቢሆንም ቀጣዩ አገዛዝ "ትሻልን ትቼ ትብስን" ዘሎ ትባባስን አምጥቶልናል። ትላንት ደርግ ያካሄደው ኢሰባዊ ድርጊት በወቅቱ በአግባቡ ፍትህ አግኝቶ ቢሆን ለቀጣይ አገዛዝ የጥንቃቄ ደወል በነበር። እንዳሰብነውም ግድያ በእኛ ባበቃ። ግና አልሆነም።

ከጥንስሡ በተንኮልና በደም የተጨማለቁት ወያኔና ሻብያ ኢትዮጵያን ለማድቀቅ ቀዳማይ ተግባራቸው ኢትዮጵያዊነትን መቅበር ነበርና ዛሬ ላይ ደርሰናል። የ27 ዓመቱ ህወሓት/ኢሕአዴግ አገዛዝ በስውር ካጠፋቸው እነ አበራሽ በርታ፣ ጸጋዬ ደብተራውና ሌሎች በአደባባይ የገደላቸው አሰፋ ማሩን መሰል

ወገኖችን አካቶ የታፈኑ፣ የት እንደደረሱ ያልታወቁ እስከዛሬ በርካቶች ናቸው። ፕሮፌሰር አሥራት ወልደየስን ለሞት ያበቃቸው ግፍ፣ እስርና ስቃይ ሳንዘነጋው በመለስ አገዛዝ የተማረረው ሕዝብ በ1997 ዓ.ም. የምርጫ ዘመን አገዛዙን ድምጽ አልባ ቢያደርገውም በወቅቱ ሥልጣን ላለመልቀቅ በተደረገው ኢሰብአዊ እርምጃ በትንሹ ወደ 200 የሚገመቱ የ12 ዓመት ሕጻናትን ጨምሮ አባትና እናት፣ በርካታ ወጣቶች በየአካባቢው፣ በየመንደሩና በየመንገዱ በመረሸን ዳግማዊ ደርግ ተከሰተ። ግንቦት 1997 እስከ ኅዳር 1998 ኢትዮጵያ ዳግም የደም መሬት ሆነች። በቀጣይነትም ምርጫን ከ99.6 ወደ መቶ በመቶ በመጠቅለል ዓይን ያወጣ አምባገነንነቱን የኢሕአዴግ አገዛዝ አሳየን።

ጊዜው ደርሷልና "እንዴት ይወድቃል?" የተባለው የወያኔ/ህወሓት አገዛዝ ከነግድያው፣ ከነግፉ፣ ከነተንኮሉ ሳይታሰብ ከራሱ በወጣ ኃይል ተቀብሮ ታሪክ ሁኖ እየተወራ፣ እየተጻፈ ነው። አገዛዝ ሲቀየር መብትና ሰላም እየሸሿት የሄደች ሀገራችን ዛሬ "እኔ አሻግራችኋለው" ያለው የጠ/ሚር ዶር ዐብይ አገዛዝ በጥሩ ሁኔታ ሀገሪቷን ወደ ደም ጎዳናና ወደ እልቂት እያሸጋገራት እያየን ነው። ዛሬ ኢትዮጵያዊነት ላይ ቆንጨራና ገጀራ ያረፈበት ወቅት ላይ ደርሰናል። የጋምቤላ፣ የደቡብ፣ የምስራቅ ሀገራችን ወገኖች በግፍ ተፈጅተዋል። ኢትዮጵያዊነት ላይ ያነጣጠረው ፍጅት አማራን ካልቀበረ እፎይታ የለውምና አንድ ዘር፣ አማራው ላይ ያነጣጠረ የዘር ፍጅት የየቀን እይታችን ከሆነ እነሆ የ27 ዓመቱ እንደተጠበቀ የሦስት ዓመቱ እግዚኦታ አያድርስ ብንለውም የጭፍጨፋው አድማሱ፣ የውድመት ዳርቻው ምን ድረስ እንደሚሆን በጨለመ ተስፋ ከሀገርና ሕዝብ ጋር እየጠበቅን ነው።

"የአባት ዳፋ ለልጅ" ባንልም የወያኔ/ህወሓት ግፍ ለትግራይ ሕዝብ ተርፎ የስቃዩ፣ የግፉ መከራ ተቋዳሽ መሆናቸው ይሰማናል። ዛሬ በሀገር ደረጃ ስንመለከተው መላ ሀገሪቷ እጅግ አሳሳቢ ሁኔታ ላይ ትገኛለች። በተለይ ኢትዮጵያዊነትን ከማጥፋት አንጻር አማራው እንዲያልቅ ተፈርዶበት አዛውንት፣ ሕጻናት፣ ወጣቶች ሳይለይ እየታረዱ፣ በተቀነባበረ መልክ አብያተ ክርስቲያናት ሲወድሙ እያየን ነው። አሸባሪነትና የዘር ፍጅት በመንግሥት ደረጃ ድጋፍ ሲያገኙ "ምን ላይ ጣለሽ ኢትዮጵያ? ምን ግፍ ሠራን አምላኬ" ያሰኛል።

"ያ ትውልድ ተቋም" የዛሬ 9 ዓመት ለሕዝብ ይፋ ያደረግነውን ድረ ገጻችን (http://yatewlid.com/ ወይም http://yatewlid.org/ )፣ ገዳይና ተገዳይ ማንና ምን እንደነበሩ፣ አገር እነማንን? እንዴት? መቼ? አጣች ለትውልዱ እልቂት መታሰቢያ ይሆን ዘንድ ማበርከታችን ይታወሳል። ያ ትውልድ ድረ ገጽ ዋናው ማዕከሉ የደርግን ዘመን ሰማዕታት አድርጎ በቀጣይ አገዛዞችም የተካሄደውን ፍጅት እንዲያካትት ሆኖ የተዘጋጀ በመሆኑ በቀጣይነት በኢሕአዴግ/ህወሓት አገዛዝ አሁን ደግሞ በብልጽግና/ኦነግ ዘመን ኢትዮጵያ ያጣቻቸውን ልጆቿን በታሪክ ማህደርነት ስለምናስገባ በዚህ አጋጣሚ ሁሉንም ኢትዮጵያዊ ወገኖቻችንን መረጃ በመስጠት ትተባበሩን ዘንድ በአክብሮት እንጠይቃለን።

በመጨረሻም እንደወጣችሁ ለጥይት እራት ለሆናችሁ፣ ከየቤታችሁ ተለቅማችሁ በየጫካው ለተጣላችሁ የ1969 ዓ.ም. ሜይ ዴይ ሰለባዎች ሁሌም እንረሳችሁም፣ ትውልድ ይዘክራችኋል፣ ያስታውሳችኋል ስንል "ያ ትውልድ ተቋም" 44ኛ ዓመት ዝክረ ሰማዕታት ጽሁፋችን ከመቃብራችሁ በላይ ይቀመጣል። እናንት የሀገርና የሕዝብ ሰማዕታት ታሪካችሁ ታሪካችን፣ ደማችሁ ደማችን በመሆኑ በቀጣይነት ትውልድ ከፍ ከፍ ያድርጋችሁ እንላለን።

በጥቅሉ በመላው ሀገራችን፣ በአስከፊው በአማራው ላይ እየተደረገ ያለውን የዘር እልቂት እጅግን እያወገዝን በትቢት የተሞላ ወያኔ/ህወሓትን ለመቅበር አምላክ ለመቀጣጫ ከጉያቸው ሳያስቡትና ባልጠበቁት መልክ የሰጣቸውን በትር አልማር ያለ አገዛዝ ዳግም በትዕቢት ታውሮ ሕዝብ እየፈጀ፣

መንደር እያወደመ ነውና ያቺ መቀበሪያ ቀን የመጣች ለታ ወየው ለገዳዮች፣ ወየው ለአራጆች እንላለን። ፍርዱ በእናንተ ላይ ይበረታልና የዚያ ጊዜ አዳኝ የላችሁምና ከወያኔ/ህወሓት አወዳደቅ ትምህርት ወስዳችሁ እኩይ ተግባራችሁን አቁሙ ምክራችንን እንለግሳለን። እውነት እውነት እንላችኋለን መጥፊያችሁን ታቃርቡታላችሁ እንጂ ሀገርና ሕዝብ ዘላለማዊ ናቸው።

የያ ትውልድ ሰማዕታት ሁሌም ይዘከሩ!!!

በአማራው ላይ የሚደረገው የዘር ፍጅት ፍትህ ያገኛል!!!

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!

ሚያዝያ 23 ቀን 2013 ዓ.ም. (May 01, 2021)

***«ያ ትውልድ ተቋም»***

Email : yatewlid@gmail.com,

ምሥለ ገጽ (Facebook) ፡ yatewlid

ስልክ ፡ (703) 300 4302

website : http://www.yatewlid.com , http://www.yatewlid.org